# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስራና ክህሎት ቢሮ

## የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና መመሪያ

መስከረም 2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ክፍል አንድ---------------------------------------------------------------------------------------------2

1. ጠቅላላ ድንጋጌዎች---------------------------------------------------------------------------------2

1. 1 አጭር ርዕስ------------------------------------------------------------------------------------2

1.2. ትርጓሜ-----------------------------------------------------------------------------------------2

1.3 ያታ አገላለፅ -----------------------------------------------------------------------------------3

1.4. የተፈፃሚነት ወሠን-------------------------------------------------------------------------------3

1.5. ዓላማ--------------------------------------------------------------------------------------------4

1.6. መርሆዎች---------------------------------------------------------------------------------------4

ክፍል ሁለት---------------------------------------------------------------------------------------------5

2. የማታ ተከታታይ ስልጠና የሠልጣኞች ቅበላ፣ የኘሮግራምና የክፍለ ጊዜ ስርጭት -----------5

2.1. የማታ ሰልጣኞች ቅበላ --------------------------------------------------------------------------5

2.2. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራምና የክፍለ ጊዜ ስርጭት -------------------5

ክፍል ሶስት---------------------------------------------------------------------------------------------6

3. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ስራዎች ተግባርና ሃላፊነት-----------------------------6

3.1. የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ወይም የኮሌጅ ዲን ተግባርና ኃላፊነት፣ ---------------------------------6

3.2. የሰልጣኝ ልማትና አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ዲን ተግባርና ኃላፊነት ------------------------6

3.3. የማታ ተከታታይ ስልጠና አስተባባሪ ተግባርና ሀላፊነት ---------------------------------------7

3.4. የሬጅስትራር ጽ/ቤት ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት-------------------------------------------------8

3.5. የትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ተጠሪዎች ተግባርና ኃላፊነት -----------------------------------9

3.6. የቤተ መጻሐፍት ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት------------------------------------------------------ 11

3.7. የአሰልጣኞች ተግባርና ኃላፊነት------------------------------------------------------------------ 11

3.8. የወርክ ሾፕ ቴክኒሽያን ተግባርና ኃላፊነት ------------------------------------------------------ 12

3.9. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና የቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ክትል ዲን ተግባርና ኃላፊነት -------- 13
3.10. የተቋም ልማትና አስተዳደር ጉዳዮች ተግባርና ሀላፊነት ---------------------------------------- 13
3.11. የተቋም ልማት አሰተባበሪ ክፍል ተግባርና ሀላፊነት ------------------------------------------- 13
3.12. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት------------ 14
3.13. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ኮሚቴ አደረጃጀት--------------------- 14
ክፍል አራት------------------------------------------------------------------------------------------------------------------ 16
4. የተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና የገቢ ምንጮች፣ የክፍያ አፈፃፀም እና-------------------- 16
የገቢ ክፍፍል ሥርዓት ---------------------------------------------------------------------------------------------------- 16
4.1. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና የገቢ ምንጮች--------------------------------------- 16
4.2. የተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ሠልጣኞች የምዝገባ ክፍያ አፈፃፀም------------------ 16
4.3. የመታወቂያ ካርድ ክፍያ አፈፃፀም ------------------------------------------------------------------- 16
4.4. የቅጣት ክፍያ አፈፃፀም-------------------------------------------------------------------------------------- 17
4.5. የሠልጣኞች ወርሃዊ ክፍያ አፈፃፀም------------------------------------------------------------------ 17
4.6. በድጋሚ ለሚሰጥ የትምህርት እና ስልጠና ማስረጃ ክፍያ አፈፃፀም------------------------ 18
4.7. የድጋሚ መረጃ ይረጋገጥልኝ አገልግሎት አሰጣጥ ክፍያ--------------------------------------- 18
4.8. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና የክፍፍል ሥርዓት----------------------------------- 18
4.9. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ወጪዎች ---------------------------------------------- 18
4.10. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ክፍያ---------------------------------------------- 19
4.11. የአሰልጣኞች አከፋፈል ስርዓት ------------------------------------------------------------------ 19
4.12. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ክፍያ የሚካቱት የኮሌጁ አሰልጣኝ እና የሚመለከታቸው አካላት አመዳደብ (ከ64%) ------------------------------------------------------------------ 19
4.13. የኮሌጅ ዲኖች፣ ምክትል ዲኖች፣ የካምፓስ ምክትል ዲኖች እና የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና አስተባባሪን ክፍያ በተመለከተ እንደሚከተለው ይሆናል --------------------- 20
4.14. በባለሙያዎች ክፍያ ውስጥ የሚካተቱ (ከ11%) ---------------------------------------------- 20

4.15. የክፍያ አፈፃፀም ቁጥጥር ሥርዓት---------------------------------------------------------------- 20

4.16. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና አሠልጣኞችና ሠራተኞች አመራረጥና የኮንትራት ቅጥር ------------------------------------------------------------------------------------------------ 20

4.17. የግማሽ ዋጋ እና ነፃ የትምህርትና ሥልጠና ዕድል የመግቢያ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ስለመስጠት------------------------------------------------------------------------------------------------- 22

4.18. ስለ ምስክር ወረቀት ------------------------------------------------------------------------------- 22

ክፍል አምስት------------------------------------------------------------------------------------------------ 23

5. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ------------------------------------------------------------------------------------- 23

5.1. የውስጥ መመሪያን ስለ ማውጣት --------------------------------------------------------------- 23

የተሻሩ ሕጎች --------------------------------------------------------------------------------------------- 23

5.2. መመሪያን ስለማሻሻል -------------------------------------------------------------------------------- 23

5.3. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ----------------------------------------------------------------------- 23

## መመሪ ቁጥር------/2018 ዓ.ም

## የመንግስት የማሰልጠኛ ተቋማት የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና መመሪያ

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጭ ለሚሰጡ የመደበኛ ትምህርትና ስልጠና አገልግሎት ይሰጣሉ። በዚህም መሰረት ይህን የትምህርትና ስልጠና ስራ ወጥና ህጋዊ አሰራር ተከትሎ እንዲፈጸም ማድረግ አስፈላጊ ነው።

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀጽ 94 መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራና ክህሎት ቢሮ ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

# ክፍል አንድ

## 1. ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. 1 አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስራና ክህሎት ቢሮ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና መመሪያ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1.2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠዉ በስተቀር በዚህ መመሪያ ፡-

1. "ከተማ  አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማለት ነው፤
2. "ቢሮ" ማለት የሥራና ክህሎት ቢሮ ነው፤
3. "ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ" በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ ከደረጃ 1 (አንድ) እስከ ደረጃ 5 (አምስት) ድረስ ትምህርትና ስልጠና እንዲሰጥ ስልጣን የተሰጠው የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ማለት ነው፤
4. "ኮሌጅ" በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮከ ደረጃ 1(አንድ) እስከ ደረጃ 4(አራት) ድረስ ትምህርትና ስልጠና እንዲሰጥ ስልጣን የተሰጠው የመንግስት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ማለት ነው፤
5. "ቅርንጫፍ ተቋማት ወይም ካምፓስ" በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ወይም ኮሌጅ ስር እንዲተዳደሩ የተቋቋሙ ተቋማት ማለት ነው፤
6. "የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና" ማለት በተለያየ ምክንያት በቀን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም የመማርና የመሰልጠን እድል የማያገኙ የከተማው ነዋሪ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ለማድረግ የተቀረጸ የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ማለት ሲሆን የመደበኛና የአጫጭር ጊዜ ስልጠና መርሐ ግብሮችን ያካተተ ነው፤
7. "የትብብር ስልጠና" ማለት ሰልጣኞች በማሰልጠኛ ተቋማት የመነሻ የንድፈ ሀሳብና የተግባር ስልጠና ከሰለጠኑ በኋላ በማሰልጠኛ ተቋማት  ከአምራች ኢንዱስትሪዎች እና

ከአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጋር በሚደረግ የውል ስምምነት መሰረት በሙያቸው በኢንዱስትሪው ውስጥ እንዲሰለጥኑ ማድረግ ነው፤

8. "የኢንዱስትሪ ውስጥ ስልጠና" ማለት በኢንዱስትሪው እና በማሰልጠኛ ተቋማት ትብብር የሚሰጥ የኢንዱስትሪ ሙያተኞችን እና በመንግስት ማሰልጠኛ ተቋማት የሚያሰለጥኑ አሰልጣኞችን ሙያዊ ብቃትን ለማሳደግ የሚሰጥ እውቀትን ከክህሎት ጋር ለማዋሀድ የሚያስችል ስልጠና ነው፤
9. “ትርፍ ሰዓት” ከመደበኛው የመንግስት የሥራ ሰዓት ውጭ ያለው ሰዓት ማለት ነው፤
10. “የትርፍ ሰዓት ሥራ” ከመደበኛው የመንግስት የሥራ ሰዓት ውጭ ባለው ሰዓት ውስጥ የሚሰራ ሥራ ማለት ነው፤
11. “የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ” ከመንግስት የስራ ስዓት ውጭ ለተሰሩ ስራዎች ስራዎቹ በጥራት መከናወናቸውን በማረጋገጥ በውሉ መሰረት አሠልጣኞችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የሚከፈል ክፍያ ማለት ነው፤
12. "አሰልጣኝ" ማለት በሙያው የብቃት ማረጋገጫ ምዘና ብቁ የሆነና የማሰልጠን ስነ ዘዴ ስልጠና ወስዶ በማሰልጠኛ ተቋም ውስጥ የሚያሰለጥን ነው፤
13. “ባለሙያ” በመንግስት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆችና ኮሌጆች ከማስተማርና ከማሰልጠን ስራ ውጭ የሆኑ ስራዎችን እንዲያከናውን የተቀጠረ ሰራተኛ ማለት ነው፤
14. «የኮንትራት ውል” አሠልጣኞች፤ወርክሾፕ ቴክኒሺያን እና ባለሙያዎች በሙያቸው ከመደበኛው ስራቸው ውጭ በትርፍ ሰዓታቸው ሥራ ለመስራት ተስማምተው ከፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ወይም ኮሌጅ ጋር የሚፈጽሙት የቅጥር የውል ስምምነት የፎርማ ሰነድ ነው፤
15. “ወርክሾፕ ቴክኒሺያን” ከፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ወይም ኮሌጅ በወርክሾፕ አቴንዳንትነት የሚያገለግል አሰልጣኝ ማለት ነው፡፡

## 1.3 *ፆታ አገላለፅ*

*ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል።*

## 1.4. የተፈፃሚነት ወሠን

*ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆችና እና ኮሌጆች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡*

## 1.5. ዓላማ

1. **የሥልጠና ተደራሽነትን ማስፋት፡-** መርሀ-ግብሩ በዋናነት የተመሰረተው በቀን መርሀ-ግብር መማር ለማይችሉ የከተማዋ ነዋሪዎች የገበያውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የሥልጠና አማራጭ በማቅረብ፣ የክህሎትና የስልጠና ተጠቃሚ ለማድረግ ነው፤
2. **የሠራተኞችን ብቃትና ማሳደግ፡-** በሥራ ላይ የሚገኙ ባለሙያዎች ዕውቀትን፣ ክህሎትንና አመለካከትን በማዳበር፣ በሥራ ገበያው ውስጥ ብቁና ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀጥሉ ከማስቻል አልፎ ወደ ሥራ ፈጠራ እንዲያመሩ ማብቃት፤
3. **የክህሎት ማሻሻያ እና ዕድገት፡-** በሥራ ላይ ያሉ ባለሙያዎች ያለባቸውን የክህሎት ክፍተት እንዲሞሉ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እንዲያውቁ እና በሙያ መሰላል ላይ ከፍ እንዲሉ የሚያስችላቸውን ተከታታይ ስልጠና እነዲያገኙ ማድረግ፤
4. **የሥራ አጥነት ቅነሳ እና ምርታማነት ማሳደግ፡-** ሠልጣኞች ያገኙትን አዲስ እውቀትና ክህሎት ወዲያውኑ ወደ ሥራ ቦታቸው እንዲያውሉ በማድረግ የግለሰብና የተቋማት ምርታማነት እና የሀገር አቀፍ የሥራ ገበያ ብቃት እንዲያድግ ማገዝ፤
5. **ተደራሽነትን ማስፋት፡-** በከተማው ውስጥ ለሚኖሩ ሁሉም የኀብረተሰብ ክፍሎች፣ በተለይም በገንዘብና በጊዜ እጦት ለሚቸገሩ፣ ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሰፊ ተደራሽነት እንዲኖር ማረጋገጥ።

## 1.6. መርሆዎች

1. በማታው ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና መርሀ-ግብር በአገሪቱ በተቀረጸው የሙያ ደረጃ መሰረት ስልጠና መስጠት፤
2. በቀኑ መርሀ-ግብር የሚከናወነው የቴክኖሎጂ ክምችትና ሽግግር በማታም በተመሳሳይ መልኩ እንዲከናዎኑ ማድረግ፤
3. በማታ ተከታታይ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም እና የቀኑ የስልጠና ፕሮግራም አንድ አይነት መሆኑን ማረጋገጥ፤
4. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሠልጣኞች ሥልጠናቸውን ካጠናቀቁ በኋላ የብቃት ማረጋገጫ ምዘና እንዲወስዱ ማብቃት፤
5. የማታው ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና የትብብር ሥልጠና አሰጣጥ በቀኑ መርሀ-ግብር ትምህርትና ስልጠና በሚተገበርበት አግባብ እንዲሆን ማድረግ።

# ክፍል ሁለት

## 2. የማታ ተከታታይ ስልጠና የሠልጣኞች ቅበላ፤ የኘሮግራምና የክፍለ ጊዜ ስርጭት

### 2.1. የማታ ሰልጣኞች ቅበላ

1. ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ ወይም ኮሌጁ የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና መርሀ-ግብር ሠልጣኞችን ተቀብሎ ለማሰልጠን የአዲስና ነባር (ከደረጃ ወደ ደረጃ) የተሸጋገሩ ሰልጣኞችን ለመቀበል የምዝገባ ፕሮግራም በማዘጋጀት ፕሮግራሙን ተመዝጋቢ ሰልጣኞች እንዲያውቁት ማድረግ፤
2. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና የአዲስ ሰልጣኞች ቅበላ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስራና ክህሎት ቢሮ ለሰልጣኞች ቅበላ ለየደረጃው ባወጣው የመግቢያ ነጥብና መስፈርቶች መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፤
3. በአጫጭር ጊዜ ስልጠና ማንኛውም ሰው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በፍላጎቱ መሰረት የስልጠና ዘርፉ በሚተምነው ዋጋ ተመዝግቦ ሊሰለጥን ይችላል፤
4. በፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆችና ኮሌጆች በቀን በሚያሰለጥኗቸው የሙያ ዓይነትና ደረጃዎች ብቻ በማታው ተከታታይ የትምህርትና ስልጠና መርሀ-ግበር ሰልጣኞችን መቀበል ይችላሉ።

### 2.2. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራምና የክፍለ ጊዜ ስርጭት

1. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ ከቀኑ መርሀ-ግብር ጋር አንድ ዓይነት ይሆናል፤
2. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና መርሀ-ግበር ከቀኑ ሥልጠና መርሀ-ግበር ጋር እንድ ዓይነት እንደመሆኑ መጠን ሰልጣኙን ብቁ ሊያደርግ በሚያስችል አግባብ ሰዓቱ ሳይሸራረፍ መሰጠት ይኖርበታል፤
3. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና መርሀ-ግበር አንድ የሥልጠና ደረጃ የሚጠናቀቀው ሰልጣኙ በተቀመጡት የብቃት አሃዶች ሙሉ በሙሉ አጠናቆ በሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና ብቁ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፤
4. የአሠልጣኞች ከፍተኛ የክፍለ-ጊዜ መጠን በሳምንት እስከ 20 (ሃያ) ክፍለ ጊዜ ሊሆን ይችላል ሆኖም ወርሀዊ ክፍለ ጊዜ ከ 80 (ሰማንያ) መብለጥ አይችልም።

# ክፍል ሶስት

## 3. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ስራዎች ተግባርና ሃላፊነት

### 3.1. የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ወይም የኮሌጅ ዲን ተግባርና ኃላፊነት፤

1. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠናን የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ወይም የኮሌጁን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፤
2. የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ ወይም የኮሌጁ የሥራ ዕቅድና በጀት የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠናን በማካተት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
3. ለማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጁ ወይም የኮሌጁ የተለያዩ ለሥልጠና አስፈላጊ በሆኑ ግብዓቶች እንዲደራጁ አመራር ይሰጣል፤
4. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና በአግባቡ መከናወኑን ይከታተላል፣ የሚታዩ የአፈፃፀም ክፍተቶችን በመለየት በወቅቱ እንዲታረሙ ያደርጋል፤
5. የኮሌጁን የትምህርትና ስልጠና ሂደት በዓመት ሁለት ጊዜ ለኮሌጁ አካዳሚክ ኮሚሽን በሚያቀርበው ሪፖርት የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠናን አካቶ ያቀርባል።

### 3.2. የሰልጣኝ ልማትና አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ዲን ተግባርና ኃላፊነት

1. የማታው ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሂደት ይመራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል ፣ይመራል፤
2. ለማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና አስተባባሪነት ለመመደብ ሶስት እጩዎችን በማቅረብ በትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን አንድ ተወካይ እንዲመረጥ ያደርጋል፤
3. ከአስተባባሪው የሚቀርቡትን ጉዳዮች ይመረምራል፣ ይወስናል፣ ከአቅሙ በላይ የሆኑትን ጉዳዮች ለዲኑ እያቀረበ እንዲወሰን ያደርጋል፤
4. የትምህርትና ስልጠና የዘርፍ ተጠሪዎች በሚያቀርቡት ሪፖርት ለሚታዩ የአፈፃፀም ክፍተቶች በወቅቱ የመፍትሄ አቅጣጫ ይሰጣል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
5. ከተቋማት ልማትና አስተዳደር ጉዳዮች እና ከኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ከቴክኖሎጂ ልማት ም/ዲኖች ጋር በቅንጅት በመስራት የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠናው ውጤታማ እንዲሆን ያደርጋል፤

6. በማታው ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና የሰልጣኝ ተወካዮችን በማወያየት በሰልጣኞች ለሚነሱ ጥያቄዎች አግባብነት ያላቸው መሆናቸውን በመለየት ምላሽ ይሰጣል፤
7. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሰልጣኞች ስራ ያላቸውና ስራ የሌላቸው መረጃዎች በአግባቡ እንዲለዩ ያደርጋል፤ ስራ የሌላቸው ከስራ ጋር እንዲተሳሰሩ ያመቻቻል፤ ይከታተላል፤
8. ከማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና አስተባባሪ በየወሩ በውሉ መሰረት በአግባቡ የተሰሩ ስራዎችን ሪፖርት በመመርመር አፅድቆ በኮሌጁ ዲን ክፍያና ሂሳብ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ክፍያ እንዲፈፀም ያስመራል፤
9. አጠቃላይ የስልጠናውን እንቅስቃሴው በየሩብ ዓመቱ ለዲኑና ለትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን ሪፖርት ያቀርባል፤
10. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ለትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን መወሰን ያለባቸውን ጉዳዮች አቅርቦ ያስወስናል፤
11. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም የነጻ ትምህርትና ስልጠና ጥያቄ የሚያቀርቡ አካላትን መረጃ እና የውሳኔ ሀሳብ ከማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ኮሚቴ በመቀበል ለትምህርትና ስልጠና ኮሚሽኑ አቅርቦ ያስወስናል፤ ውሳኔው ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤
12. የቅርንጫፍ ተቋማት ምክትል ዲን በቅርንጫፍ ተቋሙ የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥ ከሆነ ከዚህ በላይ ለሰልጣኝ ልማትና አካዳሚክ ጉዳዮች ም/ዲን የተቀመጡት ተግባርና ሀላፊነቶች ይፈጽማል።

## 3.3. የማታ ተከታታይ ስልጠና አስተባባሪ ተግባርና ሀላፊነት

1. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ክፍል ዓመታዊ ዕቅዶችን ያዘጋጃል፣ ለትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን አቅርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል፣ ይፈጽማል፤
2. 
3. የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኘሮግራም ከመጀመሩ በፊት በየደረጃው ሊኖር የሚችለውን የሠልጣኝ ቁጥር ግምት ውስጥ በማስገባት፤ከተቋም ልማት አስተባበሪ ጋር በመሆን የማሰልጠኛ ክፍሎችንና የሾፖችን ብዛት በመለየት የመቀበል አቅም ያረጋግጣል፤

4. ከየትምህርትና ሥልጠና ዘርፉ፣ ከተቋም ልማት ማሰተባበሪያ እና ከስራ ክፍሎች የሚመጣለትን የአሠልጣኞችን ፤ወርክ ሾፕ ቴክኒሺያኖችን እና ባለሙያዎች ድልድል ለሰልጣኝ ልማትና አካዳሚክ ጉዳዮች ም/ዲን በማቅረብ ያጸድቃል፤
5. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም የሰልጣኞች አመዘጋገብ፤ የኮሌጅ ውስጥና የትብብር ስልጠና አሰጣጥ ሂደት በየክፍለ ጊዜው በመቆጣጠር በስታንዳርዱ መሰረት መፈፀሙን ይከታተላል፤የሚታዩ ክፍተቶች በወቅቱ እንዲታረሙ ያደርጋል፤
6. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ላይ የሚከሰቱ የሥራ ጉድለቶች ወይም ከዲሲፕሊን ጉድለት ጋር የተያያዙ ጉዳዩችን በማጣራት ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለሰልጣኝ ልማትና አካዳሚክ ጉዳዮች ም/ዲን ሪፖርት ያደርጋል፤
7. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ላይ የሚሳተፉ አሠልጣኞችን፣ ወርክ ሾፕ ቴክኒሺያኖች እና ባለሙያዎችን የኮንትራት ውል ያሰፈርማል፤
8. ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጭ ያሉ የአጫጭር ስልጠና ሂደቶችን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፤
9. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና የሚሰጡ አሰልጣኞች በወሩ ከስልጠና ዘርፍ በሚቀርብለት ስራ ሰዓት ሪፖርት መሰረት ክፍያ እንዲፈጸም ያደርጋል፤
10. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና የሚሰጡ የተቋሙ አሰልጣኞች እጥረት በሚያጋጥምበት ጊዜ ከተቋም ውጭ የትርፍ ጊዜ አሰልጣኝ ያፈላልጋል፣ ውል ይዋዋላል፤
11. አካዳሚክ ኮሚሽን ምክትል ዲን የሚሰጡትን ተጨማሪ ተግባራት ያከናውናል።

## 3.4. የሬጅስትራር ጽ/ቤት ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

1. የማታ ተካታታይ ትምህርትና ስልጠና ነባርና አዲስ ሠልጣኞችን ለመቀበል የምዝገባ ኘሮግራም በማውጣት ሰልጣኞች እንዲያውቁት ያደርጋል፤
2. በፕሮግራሙ መሰረት መዝጋቢ ባለሙያዎችን በመመደብ አዲስና ነባር የማታ ተከታታይ ሰልጣኞች በመስፈርቱ መሰረት ለየደረጃውና በየሙያ ዓይነቱ እንዲመዘገቡ ያደርጋል፤
3. የማታ ተካታታይ ትምህርትና ስልጠና ዓመታዊ የሥልጠና ኘሮግራም በማዘጋጀት ለትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን አቅርቦ በማፀደቅ የፀደቀውን ፕሮግራም ለስልጠና ዘርፍ ተጠሪዎች በማሳወቅ ተፈፃሚ እንዲሆን ያደርጋል፤

4. የተመዘገቡ የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሰልጣኞችን መረጃ በሙያ ዓይነትና ደረጃ በማደራጀት ለትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ተጠሪዎች ያሳውቃል፤
5. በማታ ተከታታይ የስልጠና መርሀ-ግብር መሰረት ከየትምህርትና ስልጠና የዘርፍ ተጠሪዎች የሰልጣኞችን ውጤት በየሙያ ደረጃውና ዓይነቱ አረጋግጠ በመረከብ የሠልጣኞችን ውጤት (Grade) ሪፓርት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ይከታተላል፤
6. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሰልጣኞች መረጃ መሰረት ትምህርትና ስልጠናቸውን የሚያጠናቅቁ በሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና ብቁ የሆኑና ያልሆኑ ሰልጣኞችን በመለየት ብቁ ለሆኑት በሙያ ዓይነትና ደረጃ ለይቶ ዝርዝራቸውን አቅርቦ ለትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን እንዲመረቁ ያስወስናል፤
7. በተደራጀው የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሰልጣኞች መረጃ መሰረት ትምህርትና ስልጠናቸውን የሚያጠናቅቁ ሰልጣኞችን በመለየት በሙያ ደረጃውና በሙያ ዓይነቱ መሰረት የትምህርትና ስልጠና ማጠናቀቂያ ሰርትፍኬት ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፤
8. ስልጠናቸውን በተለያዩ ምክንያቶች የሚያቋርጡ የማታ ተከታታይ ስልጠና ሰልጣኞች ሕጋዊ የማቋረጥ ፎርም (Withdrawal form) በማስሞላት ይይዛል።
9. ስልጠናቸውን አቋርጠው የነበሩ ሠልጣኞች ሥልጠናውን መቀጠል ሲፈልጉ ሕጋዊ የማቋረጥ ቅፅ የሞሉ መሆኑን በማርጋገጥ ሥልጠናውን እንዲቀጥሉ ጉዳዩን ለትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን አቅርቦ በማስወሰን ውሳኔውን ለሰልጣኙ ያሳውቃል፤
10. ለማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሰልጣኞች የኮሌጁን መታወቂያ ይሰጣል፣ ያድሳል፤
11. በቅርንጫፍ የማሰልጠኛ ተቋማት የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥ ከሆነ እነርሱንም በማካተት ይሰራል።

## 3.5. የትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ተጠሪዎች ተግባርና ኃላፊነት

1. ለማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና የሚያስተምሩና የሚያሰለጥኑ አሰልጣኞችንና ወርክ ሾፕ ቴክኒሽያኖችን ይመድባል፤ ለሰልጣኝ ልማትና አካዳሚ ጉዳዮች ም/ዲን ያሳውቃል፤
2. የተመደቡት አሰልጣኞች ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ የማታ ተከታታይ ትምርህርትና ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ይከታተላል ክፍተቶች በወቅቱ እንዲታረሙ ያደርጋል፤

3. በትምህርትና ስልጠና ዘርፉ የተመደቡ ነባርና አዲስ ሰልጣኞችን ዝርዝር ከሬጅስትራር በመረከብ በማታ ተከታታይ ስልጠና ለተመደቡት አሰልጣኞች ያስተላልፋል፤
4. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሰልጣኞች ስራ ላይ ያሉና የሌሉትን በመለየት የሚሰሩት ስራ ከስልጠናው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን በመለየት የትብብር ስልጠና በሚሰሩበት የስራ ቦታ እንዲሰለጥኑ እንዲመቻች ያደርጋል፤
5. ስራ ላይ ላልሆኑ የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሰልጣኞች የትብብር ስልጠና የሚወጡባቸው እንዱስትሪዎች ከስልጠናው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው እንዱስትሪዎች እንዲለዩ ያደርጋል፤ በአግባቡ መለየታቸውን ያረጋግጣል፤
6. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና የትብብር ስልጠና የስልጠና ዕቅድ በማዘጋጀትና የስልጠና ዕቅዱን ለኢንዱስትሪው አሰልጣኝ በማሳወቅና የውል ስምምነት ሰነድ በመፈራረም እንዲፈፀም ያደርጋል፤
7. የማታ ተከታታይ የትምህርትና ስልጠና ሰልጣኞች በሰለጠኑበት የሙያ ደረጃ የተቋም ውስጥ ምዘና መዘጋጀቱንና በአግባቡ ምዘናው መካሄዱን ይከታተላል፤ ብቁ ያልሆኑት የማብቃት ስራ እንዲሰራ ያስተባብራል፣ ይመራል፤
8. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና የሚያጠናቅቁና የሚሸጋገሩ ሰልጣኞችን ውጤት ሬጅስትራር ባወጣው ፕሮግራም መሰረት ከአሰልጣኞች ሰብስቦ ትክክለኛነቱን አረጋግጦ ሬጅስትራር ጽ/ቤት ገቢ ያደርጋል፤
9. በትምህርትና ስልጠና ዘርፉ የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት የአስልጣኝ እጥረት ሲያጋጥም ከተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና አስተባባሪ ጋር በመሆን ቅጥር እንዲፈፀምላቸዉ ያደርጋሉ፤
10. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና እንዲያሰለጥኑ የተመደቡ አሠልጣኞችንና ዎርክ ሾፕ ቴክኒሽያኖችን በተመደቡት ክፍለ ጊዜ መሰረት የሥራ ሰዓት ፊርማ ይቆጣጠራል፤ በየወሩ መጨረሻ ለማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ክፍል በደብዳቤ ያሳውቃል፤
11. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት የተመደቡ አሠልጣኞች እና ዎርክ ሾፕ ቴክኒሽያኖች በተለያየ ምክንያት ስልጠና መስጠት የማይችሉ ከሆኑና ሲለቁ ወይም ከክፍል ወደ ሌላ ክፍል ሲዛወሩ ለማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ክፍል በዳብዳቤ ያሳውቃል፤

12. በቅርንጫፍ ተቋማት የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ተጠሪዎች የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥ ከሆነ ከዚህ በላይ የተቀመጡት ተግባርና ሀላፊነቶችን ይፈጽማል።

## 3.6. የቤተ መጻሐፍት ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

1. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ጊዜ ቤተ-መጻሕፍቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ መቆጣጠር፣ የንብረት ደህንነትን ያረጋግጣል፤
2. የመረጃ ምንጮች አቅርቦትና አደረጃጀት እና አስፈላጊ የሆኑትን መጻሕፍትን፣ ግብዓቶችን ለይቶ ግዥ እንዲፈጸም ማገዝ፣ እንዲሁም የተገዙትን መጻሕፍት በዘመናዊ መንገድ ካታሎግ አድርጎ ለተጠቃሚ ምቹ በሆነ መንገድ ያደራጃል፤
3. ለሠልጣኞች፣አሰልጣኞች የማጣቀሻ (Reference) አገልግሎትና የመረጃ ፍለጋ ድጋፍ መስጠት፣ እንዲሁም የቤተ-መጻሕፍቱን ሀብቶች እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ማሠልጠን፤

## 3.7. የአሰልጣኞች ተግባርና ኃላፊነት

1. የሚያሰለጥኗቸውን ነባር እና አዲስ ሰልጣኞችን ዝርዝር በመረከብ በአግባቡ ስልጠናቸውን እንዲከታተሉ ያደርጋል በየክፍለ ጊዜው ቁጥጥር ያደርጋል፤
2. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሰልጣኞችን ለማሰልጠን አስፈላጊ የሆኑ የስልጠና ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት ለሰልጣኞች ተደራሽ ያደርጋል ፤
3. በሙያ ደረጃው የተቀመጡ ዕውቀት ፣ክህሎትና አመለካከት የሚያስጨብጥ ተግባር ተኮር ስልጠና የስልጠና ስዓቱን ሳይሸራርፍ ይሰጣል፤
4. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሰልጣኞችን በየብቃት አሀዱ የተቀመጡ ዕውቀት እና ክህሎቶችን የጨበጡ መሆናቸውን በተከታታይ ምዘና እየመዘነ ያልበቁትን የክህሎት ክፍተቶቻቸውን ለይቶ ያበቃል፤
5. ስራ ላይ ያሉና የሌሉትን ሰልጣኞችን በመለየት የሚሰሩት ስራ ከስልጠናው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን በመለየት የትብብር ስልጠና በሚሰሩበት የስራ ቦታ እንዲሰለጥኑ ያመቻቻል፤
6. ስራ ላይ ላልሆኑ ሰልጣኞች የትብብር ስልጠና የሚወጡባቸው እንዱስትሪዎች ከስልጠናው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው እንዱስትሪዎች ይለያል፤

7. የትብብር ስልጠና የስልጠና ዕቅድ በማዘጋጀትና የስልጠና ዕቅዱን ለኢንዱስትሪው አሰልጣኝ በማሳወቅና የውል ስምምነት ሰነድ በመፈራረም ስልጠናው እንዲሰጥ ያደርጋል፣ ይከታተላል፤
8. ሰልጣኞች በሰለጠኑበት የሙያ ደረጃ ያሉ የብቃት አሀዶችን በማካተት በሙያ ደረጃው የተቀመጠውን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ሊለካ የሚችል የተቋም ውስጥ ምዘና በማዘጋጀት ሰልጣኞችን ይመዝናል ብቁ የሆኑት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና እነንዲወስዱ ያደርጋል ብቁ ያልሆኑት ያበቃል፤
9. ስልጠና በሚያጠናቅቁና በሚሸጋገሩ የሰልጣኞች ውጤት ባወጣው መርሀ-ግብር መሰረት የሰልጣኞችን ውጤት በአግባቡ በመሙላት ለትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ተጠሪው በወቅቱ ገቢ ያደርጋል፤
10. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና ወስደው ብቁ ያልሆኑ የማታ ሰልጣኞችን የክህሎት ክፍተት በመለየት ያበቃል፤
11. በቅርንጫፍ ማሰልጠኛ ተቋማትሰ ተቋማት ስልጠና የሚሰጥ ከሆነ ከዚህ በላይ የተቀመጡት ተግባርና ሀላፊነቶችን ይፈጽማል።

## 3.8. የወርክ ሾፕ ቴክኒሽያን ተግባርና ኃላፊነት

1. ለማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና የማሰልጠኛ ጥሬ እቃዎችን፤ የእጅ መሳሪያዎችንና ማሽነሪዎችን በወጣው የስልጠና ክፍለ ጊዜ መሰረት ለተግባር ስልጠና ዝግጁ ያደርጋል፤
2. ለማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና መርሀ-ግብር መሰረት የተግባር ስልጠናውን ከአሠልጣኝ ጋር ረዳት አሰልጣኝ ሆኖ ስልጠና ይሰጣል፤
3. ከተግባር ስልጠና በኋላ እያንዳንዱ ሰልጣኝ የእጅ መሳሪያዎችን አፅድተው በቦታቸው መመለሳቸውን ያረጋግጣል፤
4. ለማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና የስልጠና ይዘቶችን መሰረት በማድረግ ግብዓት ከማለቁ በፊት እንዲሟላ ለዘርፍ ተጠሪው ያሳውቃል፤ሲፈቀድ ከንብረት ክፍል ይረከባል፤
5. ለማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ሰልጣኞች የሚሰሩ ፕሮጀክቶች የሚቀመጡበት ቦታ ያዘጋጃል፤ ሰልጣኞች በቦታው እንዲያስቀምጡ ያደርጋል፤

## 3.9. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና የቴክኖሎጂ ሽግግር ም/ክትል ዲን ተግባርና ኃላፊነት

1. የማታ ከተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ክፍል አስተባባሪው ጋር በመሆን የማታው ትምህርትና ስልጠና የተሳካ እንዲሆን እገዛና ድጋፍ ያደርጋል፤
2. ከተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ክፍል አስተባባሪ ጋር በመሆን በሥልጠናው ሂደት ላይ የክትትልና ድጋፍ ሥራዎችን ያከናውናል፤
3. በኮሌጁ በማታው ትምህርትና ሥልጠና ክፍለ ጊዜ የሚካሄዱ የቴክኖሎጂ ክምችትና ምርምር ስራዎችን ይመራል፤ ያስተባብራል፤
4. በማታው ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ከኮሌጁ ዲን የሚሰጡትን ተጨማሪ የትምህርትና ሥልጠና ተግባራት ያከናውናል።

## 3.10. የተቋም ልማትና አስተዳደር ጉዳዮች ተግባርና ሀላፊነት

1. የማታ ከተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ክፍል አስተባባሪው ጋር በመሆን የማታው ትምህርትና ስልጠና የተሳካ እንዲሆን እገዛና ድጋፍ ያደርጋል፤
2. በማታው ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና መርሀ-ግብር አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፤
3. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሰልጠና ሰልጣኞች በወርክ ሾፕ ውስጥ ካይዘንን ተግባራዊ እንዲደረግ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
4. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሰልጠና ሰልጣኞች መረጃ በአግባቡ እንዲደራጅና ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል።

## 3.11. የተቋም ልማት አሰተባበሪ ክፍል ተግባርና ሀላፊነት

1. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ስኬታማ እንዲሆን ወርክሾፖችን ያደራጃል፤
2. የግብአት ማሟላትና የወርክሾፕ አደረጃጀትና ከማታው የሥልጠና አስተባባሪ ጋር በመተባበር፣ ለሥልጠናው አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች (መሣሪያዎች፣ ቁሳቁሶች፣ ማሽነሪዎች) በወርክሾፖች ውስጥ መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤
3. የወርክሾፕ አደረጃጀት የማታ ሰልጣኞች ልክ እንደ ቀኑ ተማሪዎች ተግባራዊ ክህሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፤

4. ሠልጣኞች በወርክሾፐ ውስጥ የካይዘን መርሆዎችን ቅልጥፍና፣ ብክነትን መቀነስና የሥራ ቦታ አደረጃጀት በተግባር እንዲያውሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
5. የሥልጠናው ተግባራዊነትና ጥራት እንዲረጋገጥ የማድረግ፤

## 3.12. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ተጠሪነቱ ለትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነት ይኖረዋል፤

1. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ከተለያዩ የስራ ክፍሎች የሚሳተፉ ባለሙያዎችን ይለያል፤
2. በክፍያ ዙሪያ የሚነሱ ጥያቄዎችን በመቀበል እየመረመረ የውሳኔ ሀሳብ ለትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን በማቅረብ ያስወስናል፤
3. ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጭ የሚሰጡ የአጫጭር ስልጠና ክፍያዎች በዚህ መመሪያ መሰረት መፈጸማቸውን ይከታተላል፤
4. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም በሰልጣኞች የሚነሱ ቅሬታዎችን ይፈታል፤ ከአቅም በላይ የሆኑት ምላሽ እንዲያገኙ ለትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን ያቀርባል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል።
5. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም የነጻ ትምህርትና ስልጠና ጥያቄ የሚያቀርቡ አካላትን በመለየት ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን ያቀርባል፤ ይከታተላል፤ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል።
6. ሌሎች ከትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

## 3.13. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ኮሚቴ አደረጃጀት

1. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም የሚከናወኑትን ተግባራት ለመደገፍ የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ኮሚቴ ይቋቋማል፤
2. የተቋቋመው የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን ሆኖ በውስጡ አንድ የመምህራን ማህበር ተወካይ፣ አንድ የማታ ሰልጣኞች ተወካይ፣ አንድ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ ተወካይ፣ አንድ

የሴቶች ጉዳይ ተወካይ እና የማታ ተከታታይ ትምህርት ስልጠና አስተባባሪን ያካተተ ይሆናል።

3. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና አስተባባሪው የኮሚቴዉ ሰብሳቢ ሲሆን ከመምህራን ማህበር የተወከለው አሰልጣኝ ደግሞ የኮሚቴው ፀሐፊ ይሆናል።

# ክፍል አራት

## 4. የተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና የገቢ ምንጮች፣ የክፍያ አፈፃፀም እና የገቢ ክፍፍል ሥርዓት

### 4.1. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና የገቢ ምንጮች

በማንኛውም የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና የገቢ ምንጭ ኮሌጁ የሚሰበስበው በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት ለከተማው ፋይናንስ ቢሮ ደረሰኝ እንዲታተምለት ጠይቆ በሚያሳትመው ደረሰኝ ብቻ ይሆናል:: መዚህም መሠረት::

1. ከማታ ሠልጣኞች የምዝገባ ክፍያ፤
2. ከማታ ሠልጣኞች የቅጣት ክፍያ ፤
3. ከማታ ሠልጣኞች ወርሃዊ ክፍያ፤
4. ከማታ ሠልጣኞች የኮሌጅ ውስጥ የማካካሻ ምዘና ክፍያ፤
5. ስልጠና ያልተወሰደባቸው የሙያ ብቃቶችን ለመሰልጠን የሚከፈል ክፍያ፤
6. ከማታ ሠልጣኞች የድጋሚ ትራንስክሪፕት መስጠት ክፍያ፤
7. ከድጋሚ ሠርተፊኬት/ዲፕሎማ መስጠት አገልግሎት ክፍያ፣
8. ከማታ ሰልጣኞች የመታወቂያ ካርድ ክፍያ እና
9. ከማታ ሠልጣኞች የድጋሚ ይረጋገጥልኝ አገልግሎት ክፍያ እና ከመሳሰሉት ይሆናል።

### 4.2. የተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ሠልጣኞች የምዝገባ ክፍያ አፈፃፀም

ማንኛውም በተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ለመሰልጠን የሚፈልግ ሠልጣኝ ኮሌጁ ያወጣውን ዝቅተኛ የመግቢያ መወዳደሪያ መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ለውድድር ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር/ ክፍሎ ተወዳድሮ ካለፈ በኋላ ለመመዝገቢያ ብር 300. 00 (ሦስት መቶ ብር) ይከፍላል።

### 4.3. የመታወቂያ ካርድ ክፍያ አፈፃፀም

ሰልጣኞች የመታወቂያ ካርድ በምዝገባ ጊዜ ብር 50.00 (ሃምሳ ብር) በመክፈል ያወጣሉ። ሠልጣኞች መጀመሪያ ያወጡት የኮሌጁ/ተቋሙ መታወቂያ ካርድ ከጠፋባቸው ፖሊስ ጣቢያ አስመዝግበው ማስረጃ ለኮሌጁ/ለተቋሙ ሲያቀርቡ ለድጋሚ መታወቂያ ካርድ ክፍያ ብር 100.00 (መቶ ብር) ይከፍላሉ።

## 4.4. የቅጣት ክፍያ አፈፃፀም

1. ሠልጣኞች ወርሃዊ ክፍያ ወር በገባ ከ1ኛው ቀን ጀምሮ እስከ 10ኛው ቀን ይከፍላሉ። ከ11ኛው ቀን እስከ 20ኛው ቀን በየቀኑ ብር 15.00 (አስራ አምስት ብር) ቅጣት በመክፈል ወርሃዊ ክፍያዉን እንዲከፍሉ ይደረጋል፤
2. አንድ ሠልጣኝ በወሩ ውስጥ መክፈል ያለበትን ወርሃዊ ክፍያ ካልከፈለ በሚቀጥለው ወር በመደበኛ ወርሃዊ ክፍያው ላይ ብር 150.00 (መቶ ሀምሳ ብር) ጨምሮ ይከፍላል፣ ሁለተኛ ወር ላይ አጠናቆ ያልከፈለ ሠልጣኝ ከሥልጠናው ይታገዳል፤
3. አንድ ሠልጣኝ በኮሌጁ የመመዝገቢያ ቀናት ውስጥ ቀርቦ ያልተመዘገበ ከሆነ በቅጣት መመዝገቢያ ወቅት በሚወጣው ማስታወቂያ መሠረት በተከታታይ ሶስት ቀናት በየቀኑ ብር 50.00 (ሃምሳ ብር) ቅጣት እየከፈለ ሊመዘገብ ይችላሉ፣ በነዚህ ቀናት ያልተመዘገበ ሠልጣኝ ከ4-10ኛው ቀን ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) እየከፈለ ይመዘገባል፣በነዚህ ቀናት ያልተመዘገበ ሠልጣኝ ከኮሌጁ ይታገዳል።

## 4.5. የሠልጣኞች ወርሃዊ ክፍያ አፈፃፀም

1. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች በተለያዩ የሙያ መስኮች ማለትም በደረጃ 1፣ በደረጃ 2፣ በደረጃ 3፣ በደረጃ 4 እና በደረጃ 5 ሥልጠና ይሰጣሉ።
2. የሠልጣኞችን ወርሃዊ ክፍያ ከዚህ በታች የቀረበ ሲሆን ለወደፊቱም እንደ ገበያው ሁኔታ ሊሻሻል ይችላል።

ለደረጃ 1 -------------------------------- ብር 350.00 (ሶስት መቶ ሃምሳ ብር)
ለደረጃ 2 -------------------------------- ብር 400.00 (አራት መቶ ብር)
ለደረጃ 3 ------------------------------- ብር 450.00 (አራትመቶ ሃምሳ ብር)
ለደረጃ 4 -------------------------------- ብር 500.00 (አምስት መቶ ብር)
ለደረጃ 5 ------------------------------- ብር 600.00 (ስድስት መቶ ብር) ነው።

3. አከፋፈሉም በየደረጃው በተቀመጠው የክፍያ መጠን ይሆናል፤
4. ሰልጣኞች ለመሰልጠን የተመዘገቡበት ደረጃ ከፍ ያለ ሆኖ ነገር ግን ስልጠና የሚጀምሩት ከደረጃ አንድ ጀምሮ በመሆኑ የሚከፍሉት ክፍያ ለሚሰለጥኑበት ደረጃ በተቀመጠው የክፍያ መጠን ይሆናል።

### 4.6. በድጋሚ ለሚሰጥ የትምህርት እና ስልጠና ማስረጃ ክፍያ አፈፃፀም

ሠልጣኞች ዋናውን ሠርተፊኬት/ቀድሞ ዲፕሎማ እና ትራንስክሪፕት ካገኙ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች ከጠፋባቸው የዋናው ምትክ ተዘጋጅቶ የትምህርትና ሥልጠና ማስረጃ የሚሰጣቸው ሆኖ፡-

- ለሠርተፊኬት ወይም የቀድሞ የዲፕሎማ ------ብር 150.00 (አንድ መቶ ሀምሳ ብር)
- ለትራንስክሪፕት------------------------ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) ይከፍላሉ።

### 4.7. የድጋሚ መረጃ ይረጋገጥልኝ አገልግሎት አሰጣጥ ክፍያ

ለመረጃ ይረጋገጥልኝ ወይም ማንኛውም የጽሑፍ አገልግሎት የሚጠይቅ መረጃ ለማግኘት ብር 150.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ብር) ለአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል።

### 4.8. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና የክፍፍል ሥርዓት

1. ማንኛውም ኮሌጅ ከማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ከሚያገኘው ገቢ 25% በመቶውን መጠቀም የሚችለው በፋይናንስ የውስጥ ገቢ ደረሰኝ ገቢ ካደረገ በኃላ በውስጥ ገቢ አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲጠቀም በተፈቀደለት መሠረት ብቻ ይሆናል፤
2. ማንኛውም ኮሌጅ ከማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና ከሚያገኘው ገቢ 75% በመቶውን ለአሠልጣኞች እና የስልጠና ስራው በቀጥታ ለሚመለከታቸው የአስተዳደር ሠራተኞች ክፍያ ሲፈፅም የወጪ ደረሰኝ ለከተማው ፋይናንስ ቢሮ እንዲታተምለት በመጠየቅና በማሳተም ሲሆን አከፋፈሉም የፋይናንስ የክፍያ ስርአትን ተከትሎ መፈፀም ይኖርበታል።

### 4.9. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ወጪዎች

1. በማታው ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ላይ ለሚሳተፉ አሠልጣኞች፤ ወርክሾፕ ቴክኒሺያኖች እና ባለሙያዎች  የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ፤
2. ለምዘና ዝግጅትና ለቢሮ የጽሕፈት መሳሪያዎች ወጭ፤
3. ለኮሌጁ አገልግሎት የሚውል ወጭ፤
4. የጥሬ ዕቃዎች (ግብዓቶች) ግዥ ወጭዎች ናቸው።

## 4.10. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ክፍያ

1. ከ 75% (በመቶ) ገቢ ውስጥ የአሠልጣኝ ድርሻ 64% (ስልሳ አራት በመቶ) ሲሆን የባለሙያዎች ደግሞ 11% (አስራ አንድ በመቶ) ድርሻ ይሆናል፤
2. ከሬጅስትራር ፅ/ቤት ሐላፊ፣ የሬጅስትራር ባለሙያዎች፣ የቤተ-መጻሐፍት አስተባባሪና ባለሙያዎች እና ከተቋም ልማት አስተባባሪ ውጭ ያሉ በአሰልጣኝ መደብ /በኬርየር ስትራክቸር / ያሉ አሰልጣኞች በ 64% (በመቶ) የሚካተቱት ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና መርሀ-ግብር ተመድበው ስልጠና ሲሰጡ ብቻ ይሆናል፤
3. በዚህ መመሪያ ያልተካተተ ያከፋፈል ስርአት በኮሌጁ በሚወሰነው የውስጥ መመሪያ የሚታይ ይሆናል።

## 4.11. የአሰልጣኞች አከፋፈል ስርዓት

ለአሰልጣኙ ከሚከፈለው 64% ውስጥ 80%ቱ ከታክስ ነጻ ሆኖ ለትራንስፖርት የሚከፈለው ሲሆን ቀሪ 20% ከደሞዝ ጋር ተጨምሮና ታክስ ተደርጎ የሚከፈል ይሆናል።

## 4.12. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ክፍያ የሚካቱት የኮሌጁ አሰልጣኝ እና የሚመለከታቸው አካላት አመዳደብ (ከ64%)

1. የኮሌጅ ዲን፣
2. የኮሌጅ እና የቅርንጫፍ ተቋማት ምክትል ዲኖችን፣
3. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና አስተባባሪ፣
4. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና የሚሰጥባቸው የዘርፍ ተጠሪዎች (ዲፓርትመንት ተጠሪዎች)፣
5. የተቋም ልማት ማስተባበሪያ ክፍሉ አስተባባሪ፣
6. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ስልጠና የሚሰጡ አሰልጣኞች፣
7. የሬጅስትራር ጽቤት ሃላፊና ባለሙያዎች፣
8. በማታው ተከታታይ ትምህርትን ሥልጠና የሚሳተፉ የቤተ-መጻሐፍት ኃላፊ እና ባለሙያዎች፣
9. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም ስልጠና በሚሰጡ ዘርፎች ያሉ የዎርክ ሾፕ ቴክኒሽያኖች ይሆናሉ።

### 4.13. የኮሌጅ ዲኖች፣ ምክትል ዲኖች፣ የካምፓስ ምክትል ዲኖች እና የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና አስተባባሪን ክፍያ በተመለከተ እንደሚከተለው ይሆናል

1. የኮሌጅ ዲኖች የ5 አሰልጣኞች ከፍተኛ ክፍያ አማካይ ይሆናል፤
2. የኮሌጅ ምክትል ዲኖች እና የካምፓስ ምክትል ዲኖች ክፍያ የ7 አሰልጣኞች ከፍተኛ ክፍያ አማካይ ይሆናል።
3. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና አስተባባሪ ክፍያ የ7 አሰልጣኞች ከፍተኛ ክፍያ አማካይ ይሆናል።

### 4.14. በባለሙያዎች ክፍያ ውስጥ የሚካተቱ (ከ11%)

ማንኛውም ኮሌጅ በአስተዳደር ዘርፍ ቀጥታ ከስልጠናው ጋር ግንኙነት ያላቸውን የስራ ክፍሎች ለይቶ በመደብና በማሰራት በሰሩት ልክ ከ 11% በመቶው ውስጥ እንዲከፈላቸው ያደርጋል።

### 4.15. የክፍያ አፈፃፀም ቁጥጥር ሥርዓት

በኮሌጁ ውስጥ ካሉት የስራ ክፍሎች ከስልጠናው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከ75% ውስጥ 64% ለአሰልጣኞች እና 11%ቱ ደግሞ ኮሌጁ መድቦ ለሚያሰራቸው የአስተዳደር ዘርፍ ባለሙያዎች እንደ ስራ አፈፃፀማቸው እና የስራ ክብደቱ በኮሌጁ የማታ ትምህርትና ስልጠና ኮሚቴ ድልድሉን ሰርቶ እንዲከፈላቸው በትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን አሰወስኖ ክፍያውን ተፈፃሚ ያደርጋል።

### 4.16. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና አሠልጣኞችና ሠራተኞች አመራረጥና የኮንትራት ቅጥር

1. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም የትርፍ ስዓት በመሆኑም ተጠቃሚ የሚሆኑት በሥራዉ ላይ የተሳተፉ አስልጠኞች፣ባለሙያዎች ብቻ ናቸው፤
2. በቀኑ መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኘሮግራም የሚሠሩ አሠልጣኞች በተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ኘሮግርም ላይ ይሳተፋሉ፤
3. የማታ ተከታታይ ትምህርና ስልጠና አስተባባሪ የቆይታ ጊዜ በየሁለት ዓመት የሚቀያየር ይሆናል፤
4. የተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ቅጥር በኮንትራት ይሆናል፤

5. አሠልጣኞችና ሠራተኞች በግልፅ ማስታወቂያ በየሥልጠና ክፍሉ ቀደም ብሎ እንዲያውቁት ከተደረገ በኋላ የቅጥር ውል ስምምነቱ በኮሌጁ ኃላፊ መፅደቅ ይኖርበታል።ለኮሌጁ አሠልጣኞች ቅጥር በሰለጠኑበት ትምህርትና ሥልጠና መስክ ደረጃቸውና ሙያ ብቃታቸው ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፤

6. አዳዲስ ተቀጣሪ አሠልጣኞች እንደነባሮች ሁሉ በማታው ትምህርትና ሥልጠና ለመቀጠር የመወዳደር መብታቸው የተጠበቀ ይሆናል።

7. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ኘሮግራም ለማሰልጠን ያመለከቱት አሰልጣኞች ዝርዝር ለትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ተጠሪዎች በማቅረብ፣ የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ተጠሪዎች እና ከአባላት ጋር በመሆን አስፈላጊውን ምርጫ ካካሄዱ በኋላ ለማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና አስተባባሪው ቀርቦ አካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ዲን ጋር በመሆን ያፀድቃል ይወስናል፤

8. በኬርየር መደብ ያሉ እና ባለሙያዎች በሚያቀርቡት ማመልከቻ መሠረት እንደ የሥራ ባሕሪያቸው እየታየ በማታው የሥልጠና ፕሮግራም ላይ በውድድር ይሳተፋሉ

9. ከኮሌጁ ውጪ አሰልጣኞችና ባለሙያዎች ስለመቅጠር፤

10. በኮሌጁ ካሉት አሠልጣኞችና ባለሙያዎች ውስጥ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዓይነትና ደረጃ የሚመጥኑ በቂ ችሎታ ያላቸው አሠልጣኞችና ባለሙያዎች ካልተገኙ በሚከተለው ቅደም ተከተል የኮንትራት ቅጥር የሚካሄድ ይሆናል፡-

11. የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ክፍል አስተባባሪው ከሚመለከታቸው የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ኃላፊዎች ጋር በመመካከር በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ተቋማት ወይም ኮሌጆች የቅጥር ጥሪ ማስታወቂያ በማውጣት ከሚቀርቡት አመልካች አሠልጣኞችና ባለሙያዎች መካከል ደረጃቸውንና የሙያ ችሎታቸውን እየመረመረ በኮንትራት ውል መቅጠር ይችላል፤

12. ይህ ካልተሟላ በሌሎች ድርጅቶችና መ/ቤቶች ግልፅ ማስታወቂያ ወጥቶ ከሚቀርቡ አመልካቾች መካከል ቅድሚያ የማሠልጠን ልምድ ያላቸው እና በምዘና ብቃታቸው የተረጋገጠውን በመምረጥ በኮንትራት ውል ይቀጥራል፤

13. የኮሌጁ የማታ ትምህርትና ስልጠና ከሚቴ ለኮሌጁ አስፈላጊ የሆኑ የሥራ መደቦችን በማጥናትና ለአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ዲን በማቅረብ ቅጥር ሊፈፅም ይችላል እንዲሁም ላገለገሉበት ግዜያት የስራ ልምድ ሊሰጥ ይችላል። አላስፈላጊ የሥራ መደቦችንም የመሰረዝ ሃላፊነት ይኖሩታል።

## 4.17. የግማሽ ዋጋ እና ነፃ የትምህርትና ሥልጠና ዕድል የመግቢያ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ስለመስጠት

1. የኮሌጁ ሠራተኞች በአንድ የስልጠና መስክ ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 5 ድረስ የማመልከቻና የመመዝገቢያ ክፍያ ብቻ ከፍለው በነፃ መሰልጠን ይችላሉ ነገር ግን ከማታዉ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ክፍያና ጥቅማ ጥቅም ማግኘት አይችሉም: ቀደም ሲል ከሰለጠኑበት ሙያ ውጪ ለመሰልጠን ከፈለጉም በራሳቸው ወጪ ይሰለጥናሉ፡ ከማታዉ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ክፍያና ጥቅማ ጥቅም ማግኘት ግን አይችሉም፤
2. የኮሌጁ ቋሚ አሠልጣኞችና ባለሙያዎች ከአብራካቸው የወጡ ልጆቻቸዉና በጉዲፈቻ የሚያሳድጓቸው/ህጋዊ ማስረጃ ሲቀርብ/ እንዲሁም በሕጋዊ የጋብቻ የምስክር ወረቀት የተረጋገጠ ባል ወይም ሚስት በነፃ ይሰለጥናሉ፤
3. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስራና ክህሎት ቢሮ መዋቅር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና መዋቅር ሥር ለሚገኙ ሠራተኞች የትምህርትና ሥልጠና ጥያቄ ሲያቀርቡ፣ በአንድ የሥልጠና መስክ ብቻ ያለ ክፍያ የሚፈቀድላቸው ሲሆን ቅድሚያ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ይሰጣል፤
4. አካል ጉዳተኞች ከማሕበራቸው ማስረጃ ሲያመጡ በትምህርትና ሥልጠና ዓመቱ መጀመሪያ ከሚመዘገቡት አጠቃላይ ሠልጣኞች 2% በግማሽ ዋጋ ሊመዘገቡ ይችላሉ። የኤች አይ ቪ ኤድስ ሕሙማን የሆኑ ሠልጣኞች ማስረጃ ሲያቀርቡ፣ በሚወሰነው መሠረት የትምህርትና ሥልጠና ዕድል /እስኮላር ሺፕ/ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

## 4.18. ስለ ምስክር ወረቀት

1. በማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም በየደረጃው ስልጠናቸውን ላጠናቀቁ ሠልጣኞች የሚሠጠው ማስረጃ ኮሌጁ እንደ የሥልጠናው ደረጃ ለቀኑ መደበኛ ትምህርትና ሥልጠና ከሚሰጠው የትምህርትና ሥልጠና ማስረጃ ጋር ተመሳሳይ ነው። ሆኖም የምስክር ወረቀቱ ስልጠና ማጠናቀቃቸውን እንጂ ብቁ መሆናቸውን አይገልጽም፤
2. ሠልጣኞች እንደ መደበኛው ስልጠና ስልጠናቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ብቃታቸውን በምዘና ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፤

# ክፍል አምስት

## 5. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

በተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና የቅበላ አቅምን በተመለከተ እንደ የሥልጠና መስኩ የሠልጣኙ ቁጥር ይለያያል። በዚህም መሠረት አዲስ ለሚመዘገቡ ሠልጣኞች የመቀበል አቅም በቀኑ ኘሮግራም ከተፈቀደው መጠን ጋር ተቀራራቢ መሆን አለበት።

### 5.1. የውስጥ መመሪያን ስለ ማውጣት

ይህንን መመሪያ ባልተቃረነ መልኩ የውስጥ አሠራር መመሪያ የማታ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ኮሚቴ በማዘጋጀት በአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ዲን በኩል ለአካዳሚክ ጉዳዮች በማቅረብ እንዲፀድቅ ያደርጋል።

## የተሻሩ ሕጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ቀደም ሲል በሥራ ላይ ያሉ የኮሌጁ አሰራሮች ሁሉ በዚህ መመሪያ ተተክተዋል።

### 5.2. መመሪያን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ በየጊዜው የሚከሰቱ ነባራዊ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ ፕሮሰስ ካውንስል ቀርቦ ሊሻሻል ይችላል።

### 5.3. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ---------2018 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።